ቀን ሚያዝያ 15 2018
Date
ቁጥር 3,1/190/18
Ref.No

በአባሪ ለተዘረዘሩት በሙሉ
ባሉበት

ጉዳዩ፡- <u>የታክስ ግዴታቸውን ባልተወጡ ድርጅቶች ላይ የማምረቻ ቦታን ለጊዜው ስለማሸግ፣ ፈቃድ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ ይመለከታል፤</u>

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርት የሚያመርቱ አምራች ድርጅቶች ግዴታቸውን ባልተወጡ ላይ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀፅ 20 እና 21 እንዲሁም በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀፅ 45(7) በተሰጠው ውክልና መነሻ በማድረግ ፣ የቅ/ፅ/ቤቶችን ግብዓትና ከህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን አስተያየት በማካተት ይህ የአሰራር እና የአፈፃፀም ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

ስለዚህ የተዘጋጀው የአሰራር ማንዋል ተግባራዊ እንዲደረግና ስራ ላይ እንዲውል እና የአሰራር ማንዋሉ 13(አስራ ሶስት) ገፅአባሪ ተደርጎ የላክን መሆኑን እያሳወቅን አምራች ፋብሪካዎች፣ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እና ሰራተኞች እንዲያውቁት እና ተገቢውን ድጋፍና ክትትል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

የጌፍ ሸፈራው
የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>

- **ለሚኒስትር ጽ/ቤት**
- **ለታክስ ስርዓት ዘርፍ**
- **ለታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት**

<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

በአባሪ የተዘረዘሩት

ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት

ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት

ለምስራቅ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለምዕራብ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለሰሜን ምዕራብ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ለባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ባህር ዳር/

ለአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /አዳማ/

ለመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /መቐለ/

ለኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/

ለሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ሀዋሳ/

ለጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ጅማ/

ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ድሬዳዋ/

ታክስ/257
22-3-18

የውስጥ ማስታወሻ

ለ፡-ታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት

ከ፡-ህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ቀን 22/03/2018 ዓ.ም

አበራ አጥላው አበበ
የህግ አገልግሎት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ጉዳዩ፡-የህግ አስተያየት ስለመስጠት፤

በኤክሳይስ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ን መሰረት በማድረግ ታክሱ በሚከፈልባቸዉ ምርት አምራች ፋብሪካዎችን ለጊዜዉ ስለማሸግ፣ ፈቃድ ስለማገድ እና ስለመሰረዝን አስመልክቶ በተዘጋጀዉ የአሰራር መመሪያ ላይ የህግ አስተያየት እንድንሰጥበት እና ግዴታቸዉን ባልተወጡ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸዉ ምርት አምራቾች የማምረቻ ፋብሪካዎቻቸዉን ለጊዜዉ ለማሸግ፣ ፈቃድን ስለማገድና ለመሰረዝ በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 45(7) መሰረት ከዚህ በፊት የተሰጠ ዉክልና ለኤክሳይስ ታክሱ ላይም ተፈጻሚ ስለመሆን አለመሆኑ የህግ አስተያየት እንዲሰጥበት በጠየቃችሁት መሰረት ተከታዩን አስተያየት ሰጥተናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የተዘጋጀዉ ረቂቅ የአሰራር ስርአት ማንዋል በኤክሳይስ ታክስ አዋጁ ላይ የተቀመጡ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጡ ዝርዝር ተግባራትና ሀላፊነትን በተለይም ኤክሳይስ ታክሱን በማያከብሩ አምራች ፋብሪካዎችን ለጊዜዉ የሚታገዱበትን ስነ-ስርአት፣ፈቃዳቸዉ ስለሚታገድበትና ስለሚሰረዝበት ሁኔታ ቀለል ባለ መልኩ ለፈጻሚዎቹ እንዲረዱት ተደርጎ የተዘጋጀ ከመሆኑም በላይ አዋጁን መሰረት ያደረገና በአዋጁ ላይ ከተቀመጠዉ መብትና ግዴታ ዉጭ በአዲስ መልክ ያካተተዉ ስልጣንና ሀላፊነት የሌለ በመሆኑ ማንዋሉን በማጽደቅ ወደስራ መግባት የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ዉክልናን በተመለከተ ለተጠየቀዉ አስተያየት ከዚህ ቀደም ከእናንተ ዳይሬክቶሬት ሚያዚያ 04 ቀን 2015 ዓ.ም በተጠየቀ ተመሳሳይ የህግ አስተያየት ጥያቄ ላይ ግንቦት 29 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ ምላሽ የህግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተሰጠዉን

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.2

አስተያየት ግልፅ ማድረግ አስፈልጓል፡፡በዚህም መሰረት በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 45(1(ሀ) መሰረት የንግድ ድርጅት ለጊዜው ከሚታሸግበት ምክንያቶች አንድ ታክስ ከፋይ በግብር ህግ መሰረት የሚፈለግበትን ሰነድ ሳይዝ ሲቀር ወይም ታክሱን በመክፈያ ጊዜው ሳይከፍል ሲቀር መሆኑን በግልጽ አመላክቷል፡፡ የግብር ህግ ማለት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 2(36) በተሰጠው ትርጓሜ መሰረት የኤክሳይስ ታክስ አዋጁን የሚጨምር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ስለሆነም በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 45(7) መሰረት የተሰጠ ውክልና በኤክሳይስ ታክስ አዋጁ መሰረት ለሚፈጸም የማሸግ ስልጣን ተግባራዊ የማይሆንበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡

በመሆኑም በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት የተሰጠው ድርጅትን ለጊዜው የማሸግ የውክልና ስልጣን ለኤክሳይስ ታክስ አዋጁ አፈጻጸምም ተግባራዊ የሚሆን መሆንኑን በመግለጽ ይህንን አስተያየት ሰጥተናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለህግ ምክርና ረቂቅ ዝግጅት ቡድን

<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.2

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 20 እና 21 መሠረት የታክስ ህግ ተገዢነትን ተፈጻሚ ለማድረግ የተዘጋጀ የአሠራር ሥርዓት

(የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታቸውን ባልተወጡት ላይ ፋብሪካን ለጊዜው ስለማሸግ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድን ስለማገድ እና ስለመሰረዝ)

ጥር /2017 ዓ.ም

አ/አበባ



መግቢያ

ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ዓይነት የቅንጦት ዕቃዎች መሠረታዊ ያልሆኑ የኢኮኖሚ ደረጃን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውሉ፣ ጉዳት የሚያስከትሉ ዕቃዎች በተጠቃሚው ጤና ማህበራዊ ኑሮ እና ኢኮኖሚ ላይ ችግር የሚያስከትሉ ዕቃዎች፣ፍጆታቸው የማይቀንስ ዕቃዎች፣ዋጋቸው በመጨመሩ ምክንያት እምብዛም የፍላጐት/የፍጆታ መቀነስ የማይታይባቸው ዕቃዎች፣የኤክሳይዝ ታክስ ከሌሎች የታክስ ዓይነቶች ካለው ልዩ ዓላማ እና ባህርይ አንጻር በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ 1186/2012 አንቀጽ 19 የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ በገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጠው ሰው ግዴታዎች፤በተጨማሪ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 17፣18 እና 19 ስለሰነዶች (መዝገብ፣ሰነዶችን ስለመመርመር፣ደረሰኞች) የመያዝ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል።

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 34 እና አንቀጽ 40 በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ ባልተሸፈኑ የኤክሳይዝ ታክስ ወንጀል እና አስተዳደራዊ ጥፋቶች በታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው ይደነግጋል።

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ 1186/2012 አንቀጽ 19፣20 እና 21 መሠረት ግዴታቸውን ባልተወጡት የኤክሳዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት አምራች ፋብሪካን ለጊዜው ስለማሸግ፣ፈቃድ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ የህግ ተገገርነት እርምጃዎች ሲሆኑ ፈቃድ የተሰጠው አምራችም በአዋጁ ከአንቀጽ 25 እስከ 28 የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ ዕቃዎች በሚመለከት የሚደረጉ የቁጥጥር አግባቦችና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው አምራች ግዴታዎች በግልጽ ተደንግጓል።

1. **የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸዉን ምርቶች የሚያመርቱ ግብር ከፋይ ግዴታዎች በተመለከተ የህግ ድንጋጌዎች፣**

1.1 በአዋጁ አንቀጽ 15 እና 16 መሠረት ማንኛውም ሰው ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት በታክስ ባለስልጣኑ መመዝገብና ፈቃድ መውሰድ የሚጠበቅበት በመሆኑ የፈቃድ ማመልከቻ በአደቀዉ ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ፣

1.2 በአዋጁ አንቀጽ 19 መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታዎች በተመለከተ

- የተሰጠውን ፈቃድ ዋና ቅጂ የንግድ ስራውን በሚያከናውንበት ዋና መስሪያ በግልጽ በሚታይ ቦታ መለጠፍ፤
- ፈቃድ የተሰጠው ሰው

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ሀ) ፈቃድ የተሰጠበትን ስራ ያቆመ እንደሆነ ፤

ለ) የተፈቀደለት አምራች የሚያከናውነውን ዋና ተግባር መጠሪያ፣ አድራሻ ሥራውን የሚያከናውንበትን ቦታ፣ ባለቤትነት ፣የመተዳደሪያ ደንብ ወይም የስራውን ባህሪ የለወጠ እንደሆነ፤

ሐ) የተፈቀደለትን አምራች የስራውን እንቅስቃሴ ለተወሰነ ጊዜ በጊዜያዊነት ያቋረጠ እንደሆነ ፣ ወይም

መ) የተፈቀደለትን አምራች በሚመለከት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የሚጠቀምበት በፈቃዱ በተመለከተው ፋብሪካ ወይም ማምረቻ እና መሳሪያ ላይ ለውጥ የተደረገ እንደሆነ፤

መረጃዎች ለታክስ ባለስልጣኑ በ7 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማስታወቂያ የመላክ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

1.3 የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ግዴታዎች በተመለከተ:

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 26 የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርን በተመለከተ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ተግባራዊ እንዲደረግ በግልጽ ተመላክቷል፡፡

1. የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በተገቢው የሂሳብ አያያዝ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የተፈቀደለት አምራች፡-

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም ጥሬ ዕቃዎችን ለመመዝገብ፣ ክብደታቸውን ለመለካት፣ ለመቆጣጠር፣ ለመቁጠር እንዲችል ወይም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተመሳሳይ የቁጥጥር ሥራዎችን እንዲያከናውን በፋብሪካው ውስጥ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያዎች እንዲኖሩ ማድረግ እና በሚገባ እንዲጠበቁ የማድረግ፣

ለ) በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የተሟላ ቁጥጥር ለማድረግ በሚያስችል መንገድ የማስቀመጥ፣

ሐ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት የጥሬ ዕቃዎችን ምዝገባ ማካሄድ፣ በተለይም በማምረት ሂደት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፋብሪካው የተረከባቸውን ጥሬ ዕቃዎች እና ግብአቶች በእነዚህ ቅፆች ላይ መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣

መ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት የመጨረሻ ምርቶችን ምዝገባ ማከናወን፣ እና በዚሁ ቅጽ ላይ በፋብሪካው የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እና ከፋብሪካው የወጡ ዕቃዎችን መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የገቢ ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ኦዲመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ሠ) የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ በዋሉ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ፣

1.4 የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድን ለማገድ በተመለከተ:

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ማገድ በተመለከተ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ተግባራዊ እንዲደረግ በአዋጁ በግልጽ ተመላክቷል።

- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 20 (1) መሠረት

ሀ) ፈቃድ ከተሰጠው ሰው የንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 19(2)(ሀ)፣(ለ)፣ ወይም (ሐ) የተዘረዘሩ ሁኔታዎች ያጋጠሙ እንደሆነ፣

ለ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተመለከተው መሠረት ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም ማናቸውንም በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ፣

ሐ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃዱ የተመለከቱ ሁኔታዎችን የጣሰ እንደሆነ፣

መ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለታክስ ባለሥልጣኑ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃን የሰጠ እንደሆነ፣

ሠ)የተፈቀደለትን አምራች በሚመለከት፣ በፈቃዱ የተመለከተው ፋብሪካ፣ ማምረቻ ወይም መጣሪያ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት ከዚያን ጊዜ በኋላ አጥጋቢ ሆነው ያልተገኙ እንደሆነ፣

- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 20 (4) ፈቃዱ የታገደ መሆኑን ማስታወቂያ የደረሰው ሰው የዕግዱ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ14 (አስራ አራት) ቀናት ውስጥ ወይም የታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ዕግዱን በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል በጽሁፍ ሊያቀርብ ይችላል።
- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 20 (5) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ዕግዱን በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን የይግባኝ ማመልከቻው በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ፣

ሀ) የይግባኙን አቤቱታ በመቀበል የፈቃዱን ዕገዳ ሊያነሳ፣

ለ) ፈቃዱ የታገደበት ሰው ዕግዱ እንዲነሳለት ለማድረግ ለዕግዱ ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን በማሟላት በማስታወቂያው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ

ኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.2 ቤተ መዛግብትና ሰነዶች አስተዳደር
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ሊያከናውናቸው የሚገባ ተግባራትን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንዲደርሰው በማድረግ፣ በማስታወቂያው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተግባራቱን ካከናወነ ዕግዱን የማንሳት፣

ሐ) ይግባኙን ውድቅ ማድረግ እና በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 21 መሠረት ፈቃዱን መሠረዝ፣ ይችላል።

1.5 <u>ፈቃድን ስለመሠረዝ</u>

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 21 መሠረት

ሀ) የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 (2)(ሀ) መሠረት ማስታወቂያ የደረሰው ከሆነ፣

ለ) አንቀጽ 20 (4) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የፈቃዱን ዕገዳ በመቃወም ይግባኝ ያላቀረበ ከሆነ፣

ሐ) በኤክሳዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 20 (5)(ለ) በተሰጠው ማስታወቂያ ወይም በታክሱ ባለሥልጣን በተሰጠ ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በማስታወቂያው የተመለከተውን ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፣

መ) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 20 (5) (ሐ) በተደነገገው መሠረት ፈቃዱ በመታገዱ ምክንያት የቀረበውን ይግባኝ የታክስ ባለሥልጣኑ ውድቅ ያደረገው ከሆነ፣

የታክሱ ባለሥልጣን ከላይ የተገለጹትን ሁኔታዎች መነሻነት ፈቃዱን ሊሠርዝ ይችላል፣

2. አስተዳደራዊ እርምጃ በተመለከተ

2.1 ከላይ በተራ ቁጥር 1 ስር የተገለጹትን በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ 1186/2012 አንቀጽ 19፣20፣21 እና የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀጽ 45 መሠረት ግዴታቸውን ባልተወጡት የኤክሳዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት አምራች ፋብሪካዎች ለጊዜው ስለማሸግ፣ፈቃድ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ ፈቃድ የተሰጠው አምራችም በአዋጁ ከአንቀጽ 25 እስከ 28 የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ ዕቃዎች በሚመለከት የሚደረጉ የቁጥጥር አግባቦች ጨምሮ የህግ ተገገርነት እርምጃዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

2.1.1 የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ በተደጋጋሚ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት የፈጸመ ሲሆን፡-

ሀ) በታክስ ሕግ መሠረት የሚፈለግበትን ሰነድ ሳይገ ሲቀር፣

- የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ በተመለከተ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.2

- ✓ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸዉን ምርቶች ለማምረት ሳይመዘገብ/ የፈቃድ ስርትፊኬት ሳይወስድ የማምረት ስራ ሲያከናውን ሲገኝ፤
- ✓ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸዉን ምርቶች ለማምረት ተመዝገቦ ፈቃድ ለመውሰድ የሚጠበቅበትን መሰፈርቶች ባለማሟላቱ በተደጋጋሚ እንዲያሟላ ምክርና ድጋፍ የሚገልጽ 3 ጊዜ ደብዳቤ የደረሰው ሆኖ ለሚሟላት ፈቃደኛ ባለመሆን እያመረቱ ያለ፤

- የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተሰጠው አምራች ግዴታዎችን ያልተወጣ፤ ህግ መሰረት የሚፈለግበትን ሰነድ ሳይዝ ሲቀር
  - ✓ ዕቃዎች ከፋብሪካው ሲወጡ ደሊቨሪ ኖት ሳይቆረጥላቸው ሲቀር፤
  - ✓ ዕቃው ሲሸጥ የሽያጭ ደረሰኝ የማይቆረጥ ከሆነ፤
  - ✓ የታክስ ማስታወቂያ በጊዜዉ የማያቀርብና የማይከፍል፤
  - ✓ የግብአትና የምርት መቆጣጠሪያ መዝገቦችን አለመያዝ፤
  - ✓ የጥሬ ዕቃዎች፣ በምርት ሂደት ላይ ያሉ እና ያለቀለት ምርት ቆጠራ ሰነዶችን የማይዝ፤
  - ✓ ደረጃዉን የጠበቀ የሂሳብ ሪፖርት ያለማቅረብ፤
  - ✓ ለቁጥጥር አመች የሆኑ የውስጥ ለውስጥ መረካከቢያ ሰነዶችን አሳትሞ/በሲስተም አለመጠቀም እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን ያለማቅረብ፤

  ለዚህም እንዲያሟላ 3 ጊዜ በተጻፈ ማስጠንቀቂያ /ማሳሰቢያ የደረሰው ሆኖ ያላስተካከለ፤

ለ3 ተከታታይ የሂሳብ ጊዜ ታክሱን በመክፈያ ጊዜው ሳይከፍል ሲቀር ይሆናል።

2.2 የንግድ ድርጅት ለማሸግ ማስጠንቀቂያ ስለሚሰጥበትና ተፈጻሚነት በተመለከተ

2.2.1 የማሸጊያ ትዕዛዝ የሚሰጠው በሚኒስትሩ (በዋና ዳይሬክተሩ) የማሸጊያ ትዕዛዝ ለመስጠት በሚኒስትሩ (በዋና ዳይሬክተሩ) ስልጣን በተሰጠው ስራ አስኪያጅ ብቻ ነው።

2.2.2 ታክስ ከፋዩ ታክሱን ካልከፈለ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ እንዲይዝ 3 ጊዜ ማሳሰቢያ/ማስጠንቀቂያ ደርሶት ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ7(በሰባት) ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዩን የንግድ ድርጅት ለ14 (አስራ አራት) ቀን በጊዜያዊነት የሚያሸግ መሆኑን የሚገልፅ ውክልና በተሰጠው የተፈረመ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.2

2.2.3 ከላይ በተራ ቁጥር 2.2.2 በተገለጸው መሠረት ታክስ ከፋዩ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ታክሱን ካልከፈለ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ ካልያዘ ወይም ግዴታዉን ካልተወጣ ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዩን የንግድ ድርጅት ከ14 (አስራ አራት) ቀን ላልበለጠ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲታሸግ የሚያደርግ ትዕዛዝ ውክልና በተሰጠው የተፈረመ ("የማሸጊያ ትዕዛዝ") ይሰጣል፡፡

2.2.4 ባለስልጣኑ ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት መግባት የሚችል ሲሆን የማሸጊያ ትዕዛዝ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ የፖሊስ መኮንን በቦታው እንዲገኝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2.2.5 ባለስልጣኑ በማሸጊያ ትዕዛዝ መሰረት በታሸገው የታክስ ከፋዩ ንግድ ድርጅት ህንፃ ላይ ፊት ለፊት በሚታይ ቦታ የሚከተሉትን ቃላት የያዘ ማስታወቂያ ይለጥፋል፡- "የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 45 መሰረት በባለስልጣኑ ትዕዛዝ ለጊዜው ታሽጓል"፡፡

2.2.6 የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት እንደገና እንዲከፈት ያደርጋል፡-

ሀ. ሚኒስትሩ ወይም ውክልና የተሰጠው ሰራተኛ ታክስ ከፋዩ የኤክሳይዝ ታክስ የፈቃድ ስርትፊኬት ለመውሰድ ወይም በህጉ መሰረት የሚፈለግበትን ሰነድ ለመያዝ የሚያስችል በቂ እርምጃ ወስዷል ብሎ ሲያምን፤

ለ. ታክስ ከፋዩ ታክሱን የሚከፍል ከሆነ፤

ድርጅት በሚታሸግበት ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

- የድርጅቱ ባለቤት፣ ስራ አስኪያጅ ወይም እነሱ የወከሉት ባለበት ሁኔታ የማሸግ ስነ-ስርዓቱን ማከናወን፣
- የሚበላሹ ግብዓት/ጥሬ ዕቃዎች እና ምርቶችን ማስወጣት፣
- በሚታሸግበት ወቅት የነበሩ ግብዓት/ጥሬ ዕቃዎች ፣በሂደት ላይ ያሉ ምርቶች እና የተመረቱ ምርቶችን መቁጠርና መተማመኛ ቅፅ ላይ ማስፈረም፡፡

2.3 የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድን ማገድና መሠረዝ ተፈጻሚ ለማድረግ ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀፅ 20 እና 21 እንደተደነገገዉ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድና ቁጥጥር ግዴታዎቹን የማይወጣ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸዉን ምርቶች የሚያመርት ድርጅት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ሚኒስቴር
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.2

በመጀመሪያ የንግድ ድርጅትን በጊዚያዊን በማሸግ በሚወሰድ አሰተዳደራዊ እርምጃ ያላስተካከለ እንደሆነ ወይም ማሸግ ሳያስፈልግ ከዚህ በታች እንደተገለጸዉ የታክስ ባለስልጣኑ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃዱን ማገድ /ወይም መሠረዝ ይችላል፡፤

2.3.1 የታክስ ባለሥልጣኑ የተሰጠውን ፈቃድ ለማገድ ወይም ለመሠረዝ ያቀደ እንደሆነ፣ ባለፈቃዱ ሊወሰድ የታቀደውን እርምጃ እንዲያውቀው ከ21 ቀናት በፊት በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የተፈረመ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡

2.3.2 ይህን ማስጠንቀቂያ እርምጃው እንዲወሰድ መንስኤ የሆኑትን ሁኔታዎች እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው ማስተካከያ ሊያደርግባቸው የሚገባ ጉዳዮችን ጭምር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

2.3.3 የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድን ያገደ እንደሆነ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ፈቃዱ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የተፈረመ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

2.3.4 ፈቃድን ለማገድ የተሰጠ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው ፈቃዱ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ በጽሁፍ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

2.3.5 የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ 20 (5) በ14 ቀናት ጊዜ ውስጥ የተገለጹትን እርምጃዎች ካልወሰደ የፈቃዱ ዕገዳ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

2.3.6 የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት ባለመፈጸሙ የአምራቹ የኤክሳዝ ታክስ ፈቃዱ የሚሰረዝ ከሆነ በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የተፈረመ በጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ፈቃዱን ሊሠርዝ ይችላል፣

2.3.7 የፈቃድ መሠረዝ ተፈፃሚ የሚሆነው ፈቃዱ መሠረዙን በሚገልጸው ማስታወቂያ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ነው፡፡

2.3.8 ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የተሰጠውን ፈቃድ መሠረዝ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈልን እና የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብን ጨምሮ ፈቃዱ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ባከናወነው ወይም ባላከናወነው ማናቸውም ተግባር ምክንያት በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የሚኖርበትን ተጠያቂነት አያስቀረዉም፡፡

- የኤክሳዝ ታክስ አምራች የንግድ ድርጅትን በጊዚዊነት ማሸግ፣ፈቃድን ስለማገድና ፈቃድን ስለመሠረዝ ቅያች ከዚህ በታች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡



ቁጥር----------

ቀን----------

ለ .....

<u>የንግድ ድርጅት የማሸጊያ ትዕዛዝ</u>

በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር.....በተ.እ.ቁ.....በኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ቁጥር ..... ተመዝግበው የሚገኝ የ----------ቅ/ጽ/ቤታችን ግብር ከፋይ መሆንዎ ይታወቃል፡፡

በተደጋጋሚ----------

---------- በተደረገ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርና ክትትል በቀን.....የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ በቀን ..... ሁለተኛ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም በቀን.....ሶስተኛ ማስጠቀቂያ ተሰጥዎታል፡፡ ነገር ግን በድርጅታችሁ ላይ የታዩትን ችግሮች በ7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ የማታስተካክሉ ከሆነ ድርጅትዎ ለ14 (አስራ አራት) ቀናት በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀጽ 45 መሠረት የሚታሸግ መሆኑን እየገለፅን ይህ የማሸጊያ ትዕዛዝ ተሰጥቷችኋል፡፡

ከሠላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ቁጥር----------

ቀን----------

ለ .....

ድርጅትን ለጊዜው ስለማሸግ

በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር.....በተ.እ.ቁ.....በኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ቁጥር ..... ተመዝግበው የሚገኝ የ----------ቅ/ጽ/ቤታችን ግብር ከፋይ መሆንዎ ይታወቃል።

በተደጋጋሚ----------

---------- በተደረገ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርና ክትትል በቀን.....የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ በቀን ..... ሁለተኛ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም በቀን.....ሶስተኛ ማስጠቀቂያ ተሰጥዎታል። ነገር ግን በድርጅታችሁ ላይ የታዩትን ችግሮች ለማስተካከል ፈቃደኛ ባለመሆንዎ ድርጅትዎ ለ14 ቀናት በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 45 መሠረት በባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ለጊዜው ታሽጓል።

ከሠላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ቁጥር----------

ቀን----------

ለ .....

ፈቃድን ስለማገድ

በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር.....በተ.እ.ቁ.....በኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ቁጥር ..... ተመዝግበው የሚገኝ የ----------ቅ/ጽ/ቤታችን ግብር ከፋይ መሆንዎ ይታወቃል።

በተደረገዉ የኤክሳዝ ታክስ ቁጥጥር ወይም ምርመራ በተገኙት የኤክሳዝ ታክስ ፈቃድ ወይም ቁጥጥር ግዴታዎችን ባለማሟላቶ በ----------ቀን ለ14 ቀናት ድርጅቶ ለግዛዊነት በመታሸጉ አስፈላግውን የማተካከያ እርምጃ ባለ መውሰዶ / በተደረገ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርና ክትትል በቀን.....የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ በቀን ..... ሁለተኛ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም በቀን.....ሶስተኛ ማስጠቀቂያ ተሰጥዎት በድርጅታችሁ ላይ የታዩትን ችግሮች ለማስተካከል ፈቃደኛ ባለመሆንዎ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃዶ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 20 መሰረት የድርጅቶ ኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ለ14 ቀናት የታገደ መሆኑን እናስታዉቃለን ::

ከሠላምታ ጋር



ቁጥር ----------

ቀን----------

ለ .....

ፈቃድን ስለመሰረዝ

በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር.....በተ.እ.ቁ.....በኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ቁጥር ..... ተመዝግበው የሚገኝ የ----------ቅ/ጽ/ቤታችን ግብር ከፋይ መሆንዎ ይታወቃል።

በደብዳቤ ቁጥር---------- በቀን---------- ባቀረባችሁት የይሰረዝልኝ ማስታወቂያ ወይም በ----------ቀን ለ14 ቀናት ድርጅቶ ለግዛዊነት በመታሸጉ ችግሮች ለማስተካከል ፈቃደኛ ባለመሆንዎ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃዶ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 21 መሰረት የተሰረዘ መሆኑን እናስታውቃለን።

ከሠላምታ ጋር



ከምዝገባና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች(101)

- ከምዝገባና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች ተፈጻሚ የሚሆኑት በህግ የመመዝገብ ግዴታ ላለባቸው እንዲሁም ስራቸውን ሲያቆሙ ምዝገባው እንዲሰረዝ የማድረግ ግዴታ ለተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ነው፡፡
  - ✓ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ለምዝገባ እስከ አመለከተበት ወይም በባለስልጣኑ አነሳሽነት እስከ ተመዘገበበት ቀን ድረስ መክፈል ያለበትን ታክስ 25%
  - ✓ የሚከፍለው ታክስ ከሌለ ብር 1000 ይከፍላል፡፡ ሌላው ግን የሚጣለው 25 በመቶ ቅጣት ከ 1000 ብር የሚያንስ ከሆነ የሚከፍለው 1000 ብር ነው፡፡
  - ✓ ላለመመዝገቡ ወይም ምዝገባውን ላለማሰረዙ በቂ ምክንያትነት ካቀረበ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ አይሆንበትም፡፡
- ለአዋጁ አንቀጽ 101/04/ አፈጻጸም **በቂ ምክንያት** ማለት ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፍልበትን የንግድ ስራ ካቆመ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች የሚከሰቱ አደጋዎች ያጋጠመ እንደሆነ፣ ታክስ ከፋዩ ወይም የታክስ እንደራሴ በጽኑ ህመም ላይ የሚገኙ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ እንደሆነ ነው፡፡

የታክስ ከፋዩ ግዴታዎች

ማንኛውም የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች አሉበት፤

- አግባብ ባለው የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት የታክስ ባሥልጣኑ በሚፈቅደው ዓይነት የሒሳብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶች ይይዛል፡፡
- ከታክስ ባለሥልጠኑ በሚሰጠው ቅጽ ላይ ታክሱን በሚገባ ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሚሆነውን መረጃ የሚያሳይ መግለጫ ሞልቶ በየወሩ ለታክስ ባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡
- በታክስ ባሥልጣኑ ወኪል በሥራ ቦታው በመገኘት ስለታክስ አሰባሰብ ለሚያደርገው ቁጥጥር አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ አሟልቶ ያቀርባል፡፡
- የሥራውን ዓይነትና የሥራውን አድራሻ እንዲሁም ሥራውን ሲጀምር ወይም ሲያቋርጥ የሚፈልግበትን ታክስ በሙሉ ሥራውን ባቋረጠ በ30 ቀናት ውስጥ አጠናቆ ይከፍላል፡፡
- ለውጦችን ሰለማስታወቅ ለባለሥልጣኑ ወደያውኑ ያሳውቃል፡፡
- ማናቸውም ታክስ ከፋይ ስሙ ፣አድራሻው ፣የንግድ ሥራው ቦታ፣ አደረጃጀቱ ወይም ታክስ የሚከፈልበትን ዋንኛው የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ወይም የሚያከናውናው ተግባራት

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ዓይነት እና ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚከናወንበትን አድራሻ ወይም ስም የቀየረ እንደሆነ ይህንኑ ለታክስ ባለሥልጣኑ በ21 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማስታወቅ አለበት፡፡

2.5. የኤክሳይዝ ታክስ በወቅቱ አስታውቆ አለመክፈል /ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ውጤት

ግብር ከፋዩ የሰበሰበውን የኤክሳይዝ ታክስ ከላይ በየግብር ከፋዩ ደረጃ በተገለጸው የመክፈያ ጊዜ አስታውቆ ኤክሳይዝ ታክሱን ካልከፈለ ታክሱን ባለማስታወቅ በየወሩ 5% እየታሰበ 25% እስኪሞላ ድረስ መቀጫ እየታሰበ መቀጫው ከታክሱ ጋር ይወሰናል፡፡ ባልተከፈለው ኤክሳይዝ ታክስ ላይ የሚታሰበው ወለድ የማስከፈያ ልክ በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛ የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ ላይ 15% ታክሎበት በሚገኘው ምጣኔ መሠረት ወለድ ታስቦ ኤክሳይዝ ታክስ ጋር ተዳምሮ ይወሰናል ፡፡

